# ቀዶ ጥገናውን ለማካሄድ መዘጋጀት

ይህ መመርያ ከቀዶ ጥገና በፊትና በኃላ ያለውን እያንዳንዱ ሂደት እንዴት መዘጋጀት እንዳለብዎት ይገልጻል፡፡ ጥያቄ ካልዎት በቅድመ ቀዶ ህክምና ቃለ መጠይቅ ወቅት ከቀዶ ጥገና ሐኪምዎ ወይም የእንክብካቤ ቡድንዎ ጋር ያናግሩ፡፡

**በዚህ ሰነድ በሚከተሉት ጉዳያዎች መረጃ ያገኛሉ**


- የቅድመ-ቀዶ ጥገና መከታተያ
- ቅድመ ሂደት ግምገማ
- የመፆም መመርያ
- ቅድመ-ቀዶ ጥገና የቆዳ ዝግጅት
- በሚደርሱበት ሰዓት የሚኖርዎት ዕቅድ
- በቀዶ ህክምናዎ ቀን ምን ያደርጋሉ
- ከቀዶ ጥገናዎ በኃላ ምን ይጠብቃሉ
- ለቀዶ ጥገና መክፈል
- ቦታዎች


---

## የቅድመ-ቀዶ ጥገና መከታተያ

ስለቀጣዩ የቀዶ ጥገና ሂደት መረጃ ለማግኘት ይህንን የመከታተያ ዝርዝር ይጠቀሙ፡፡ ጥያቄዎች ካሉዎት እባክዎን የመረጡትን የ Inova ቅድመ-ቀዶ ጥገና ግምገማ ክሊኒክ ያነጋግሩ፡፡

☐ የህክምና መጠይቅዎ በተቻለ ፍጥነት በ MyChart ይሙሉ፡፡ የ MyChart አካውንት ከሌልዎት በInova.org/MyChart ይመዝገቡ

☐ ቀዶ ጥገናዎ እስኪደርስ ወይም በኃላ አዲስ የ GLP-1 ህክምና (እንደ Wegovy®፣ Ozempic®፣ Mounjaro®፣ Zepbound® ወይ ሌሎች) አይጀምሩ

☐ የቀዶ ጥገና ቀንዎ ወይም ሰዓቱ ከተቀየረ ከቀዶ ጥገናዎ አንድ የስራ ቀን በቀደም ብሎ ከቀዶ ጥገና ሐኪምዎ ቢሮ የሚደውልልዎትን የስልክ ጥሪ ይጠብቁ

☐ ወደ ቀዶ ጥገና ሐኪም የሚደውሉት
- ቀዶ ጥገናዎ ፕሮግራም የሚቀየር ወይም የሚሰረዝ ከሆነ
- ካመምዎት ወይ ሙቀት ከተሰማዎት (እስከ ቀዶ ህክምና ቀንዎ አይጠብቁ)

**72 ሰዓትት ከቀዶ ህክምናዎ በፊት**

☐ በዚህ ሰነድ የአመጋገብ መመርያዎች ማየትዎን ያረጋግጡ

☐ በዚህ ሰነድ ያሉ የህክምና መመርያዎች ማየትዎን ረጋግጡ

# የቅድመ ቀዶ ጥገና ግምገማ

በቀዶ ጥገና ግምገማ ወቅት እኛ

- የህክምና፣ መድሀኒት ታሪኮን መገምገምና ማንኛውንም የሚያስፈልጉ ምርመራዎችን ማካሄድ
- የምርመራ ውጤት መገምገምና ከእንክብካቤ ቡድን ጋር በመሆን ክትትል ማቀናጀት
- ሁሉም Inova ሰነዶችና ተጨማሪ መረጃዎች መሞላታቸውን ማረጋገጥ
- መጾም እና መድሃኒቶችን ጨምሮ የቅድመ ቀዶ ጥገና እና የሂደት መመሪያዎችን ማቅረብ
- ጥያቄዎችዎን እንመልሳለን

ከቀዶ ጥገና ህክመናው በፊት የሚደረገው ቃለ መጠይቅ በአብዛኛው ከ30 እስከ 90 ደቂቃ የሚወስድ ሲሆን በስልክ፣ በቪርቹዋል ወይም በአካል በመገኘት ሊካሄድ ይችላል፡፡ እባክዎ ቀጠሮውን በተቻለ ፍጥነት ያስይዙ፡፡ እባክዎ አስተርጓሚ ከፈለጉ ቀጠሮ በሚያስይዙበት ጊዜ ያሳውቁን፡፡

**ቅድመ ሂደት ግምገማ ቀጠሮ ቀን፡**

**ቅድመ ሂደት ግምገማ ቀጠሮ ሰዓት፡**

**ቅድመ ሂደት ግምገማ ቦታ (እባክዎትን አንድ ይምረጡ)**

☐ Inova Pre-Procedural Evaluations – Alexandria
4320 Seminary Rd.
Alexandria, VA 22304
ስልክ፡ 703-504-7880

☐ Inova Pre-Procedural Evaluations – Willow Oaks (Fairfax)
8260 Willow Oaks Corporate Dr. #650
Fairfax, VA 22031
ስልክ፡ 703-776-2000

☐ Inova Pre-Procedural Evaluations – Fair Oaks
3700 Joseph Siewick Dr., #100
Fairfax, VA 22033
ስልክ፡ 703-391-4809

☐ Inova Pre-Procedural Evaluations – Loudoun
44045 Riverside Pkwy. #165
Leesburg, VA 20176
ስልክ፡ 703-858-8192

☐ Inova Pre-Procedural Evaluations – Mount Vernon
2501 Parkers Ln.
Alexandria, VA 22306
ስልክ፡ 703-664-7545

# የመፆም መመርያ

የህክምና ሂደትዎ በአንስቴዢያ ወይ ሴዳሽን የሚካሄድ መሆኑ መመርያዎቹን በጥንቃቄ ይከታተሉ፡፡ የእነዚህ መመርያዎች የመያከተሉ ከሆነ ለችግር የመጋለጥ ዕድል የሚያሰፋና ቀዶ ጥገናዎች እንዲዘገይ ወይም ሌላ ቀጠሮ እንዲሰጥዎት ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ጠቃሚ ምክሮች

- **ቀዶ ጥገናዎ እስኪደርስ ወይም በኃላ አዲስ የ GLP-1 ህክምና** (እንደ Wegovy®፣ Ozempic®፣ Mounjaro®፣ Zepbound® ወይ ሌሎች) አይጀምሩ፡፡
- **ባለፉት 5 ሳምንታት የ GLP-1 ህክመና ካቆሙ** የ GLP-1 ልዩ አመጋብ የጾም መመርያዎች መከተል አለብዎት፡፡ ከቀዶ ህክምና በፊት ይህን መድኃኒት መውሰድዎን እንዳቆሙ እባክዎ ለሕክምና አቅራቢዎ ያሳውቁ፡፡
- **የሆድ ባዶ መሆን የሚዘገይባቸው ታካሚዎች** ከተያዘላቸው የቀዶ ጥገና መርሃግብር 48 ሰዓት በፊት ጀምሮ ዝቅተኛ ስብ ያለውን እና በቀላሉ የሚፈጭ ምግብ መግብ መመገብ አለባቸው፡፡
- **ረዘም ላለ ጊዜ መጾም ጥሩ ሲሆን ችግር እንደይከሰት ይከላከላል፡፡** የቀዶ ጥገና ሐኪምዎ በእነዚህ መመሪያዎች ከተገለጸው በላይ ለረዘም ያለ ጊዜ እንዲጾሙ ካዘዞዎት የሐኪሙን መመሪያ ይከተሉ፡፡ የጾም ጊዜው ከዚህ አጭር ከሆነ በዚህ ሰነድ ውስጥ የተገለጹትን መመሪያዎች ይከተሉ፡፡

### መደበኛ የጾም መርሃ ግብሮች

| ተስማሚ ጊዜ | መመርያዎች |
|---|---|
| **11 ፒኤም ምሽት** ከቀዶ ጥገና በፊት | ያልተፈጨ ምግብና ንጹህ ያልሆነ ፈሳሽ መወሰድ ያቆሙ፡፡<br>*ከዚህ በኃላ የሚፈቀዱ ንጹህ መጠጦች መውሰድ ይችላሉ(ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል)፡፡* |
| **6 ሰዓትት** ከቀዶ ህክምናዎ በፊት | ለህጻናት ፎርሙላ መጠቅም ያቁሙ |
| **4 ሰዓትት** ከቀዶ ህክምናዎ በፊት | ለህጻናት የእናት ጡት ወተት ያቁሙ |
| **2 ሰዓትት** ከቀዶ ህክምናዎ በፊት | ሁሉም በአፍ የሚወሰድ ያቁሙ |

### GLP-1 እና ሆድ ባዶ መሆን መዘግየት ያለባቸው ታካሚዎች የጾም መስፈርቶች

| ተስማሚ ጊዜ | መመርያዎች |
|---|---|
| **24 ሰዓትት** ከቀዶ ህክምናዎ በፊት | ከቀዶ ሕክምናዎ ሰዓት በፊት ለ24 ሰዓታት ደረቅ ምግቦችን ሾርባን ወይም ንጹህ ያልሆኑ ፈሳሾችን አይመገቡ ወይም አይጠጡ፡፡ *ከቀዶ ሕክምናዎ ሰዓት በፊት ባሉት 24 ሰዓታት ውስጥ የተፈቀዱ( ከታች የተዘረዘሩትን) ንጹህ ፈሳሾችን ብቻ መጠጣት ይችላሉ፡፡ የቀዶ ጥገና ህክምናዎ ሰዓት ካላወቁ ከቀዶ ጥገና አንድ ቀን በፊት ከጠዋቱ 7 ኤኤም ጀምሮ ደረቅ ምግቦች፣ ሾርባን ወይም ንጹህ ያልሆኑ ፈሳሾችን መመገብ እና መጠጣት ያቁሙ፡፡* |
| **8 ሰዓትት** ከቀዶ ህክምናዎ በፊት | ከፍተኛ የካርቦ ሃይድሬት መጠን ያላቸው መጠተች (እንደ Clear Fast® እና Ensure Pre-Surgery Clear Carbohydrate Drink) ያሉ መጠጣትዎን ያቁሙ |
| **4 ሰዓትት** ከቀዶ ህክምናዎ በፊት | ሁሉም በአፍ የሚወሰድ ያቁሙ |

***የንጹህ መጠጦች ማብራርያ፡*** *ውሃ፣ የአፕል ጭማቂ፣ የስፖርት መጠጦች (እንደ Gatorade® ያሉ) ጥቁር ቡና ወይም ሻይ ያለ ወተት፣ ከሬም ወይም ማር፡፡*

# የቀድሞ ቀዶ ጥገና የቆዳ ዝግጅት መመርያዎች

የኢንፌክሽን አደጋን ለመከላከል ከቀዶ ጥገኛ በፊት ቆዳዎ **ክሎርክሳይድ ግሉኮንት (Chlorhexidine Gluconate (CHG))፣ 4%፣** በተባለ ጀርም ገዳይ ውሁድ ይታጠቡ::

## CHG መቼ ይወስዳሉ

**ለአብዛኛወቹ ቀዶ ጥገኛዎች**
**ሁለት** ጊዜ ይታጠቡ

- አንዱ ቀደም ብሎ ከቀዶ ጥገና ሌሊት
- አንዱ በቀዶ ጥገናው ጥዋት

**ለአከርካሪ አጥንት ወይም ለጋራ ምትክ ቀዶ ጥገና**
**ሶስት** ጊዜ ይታጠቡ:

- ከቀዶ ጥገና ህክምናው በፊት ባሉት እያንዳንዱ ሌሊት
- አንዱ በቀዶ ጥገናው ጥዋት

## CHG የት መግዛት አለብዎት

በሁሉም የመድሃኒት መስጫዎች ይገኛል-ማዘዣ አያስፈልግም:: የተለመዱ የብራንስ ስሞች Hibiclens፣ Hibistat፣ Exidine እና Hex-A-Clens ናቸው:: ድጋፍ ካስፈለግዎት የፋርማሲ ባለሙያ ይጠይቁ::

**በአማካይ አንድ ጊዜ ለመታጠብ ከ2-4 ኦንስ CHG ያስፈልግዎታል::**

## CHG የደህንነት ምክሮች

- እገዛ አስፈላጊ ከሆነ ረዳቱ በመጀመሪያ እጃቸውን በደንብ መታጠብ አለበት::
- CHG በመታጠቢያው ውስጥ ብቻ ይጠቀሙ:: ገላውን መታጠብ የማይቻል ከሆነ አማራጭ መመሪያዎችን ለማግኘት የቀዶ ጥገና ሃኪምዎን ያነጋግሩ::
- የመቅላት፣ ሽፍታ ወይም የቆዳ መቆጣት ካስተዋሉ CHG መጠቀምዎን በማቆም የቀዶ ጥገና ሃኪምዎን ያነጋግሩ::
- በ CHG ታጠቡ በኃላ ከቤት እንስሳት የቅርብ ንክኪ ያስወግዱ፤ እንስሳቱ ቫክተርያ ሊያስተላልፉ ችላሉ::

## CHG እንዴት መጠቀም ይቻላል

1. በመደበኛ ሳሙናዎ እና ሻምፖዎ ይታጠቡ፤ ከዚያም ሙሉ በሙሉ ይታጠቡ::
2. ውሃውን ያጥፉ እና CHG በእጆችዎ ይቀቡ (የማጠቢያ ጨርቅ ወይም ስፖንጅ አይጠቀሙ):: ***ፊትዎን፣ የራስ ቆዳዎን እና የመራብያ አካባቢዎን እንዳይነካ ያድርጉ::*** *የአንገል ወይም የጭንቅላት ቀዶ ሕክምና የሚደረግልዎ ከሆነ የእንክብካቤ ቡድንዎ የሰጠዎትን መመሪያ ይከተሉ::*
3. መላውን ሰውነትዎን በተለይም ቀዶ ጥገና በተደረገበት አካባቢ - ለ **3 ደቂቃዎች** ቀስ ብለው ይሹት::
4. CHG ሙሉ በሙሉ ይለቅልቁት::
5. በንጹህ ፎጣ ያድርቁት::
6. ሎሽን፣ ዴድራንት ወይም ሽቶ አይቀቡ::
7. ንጹህ ፒጃማ ወይ ልብስ ይልበሱ::
8. ቀዶ ጥገና ባደረጉበት ጠዋተ እነዚህን ሂደቶች ይድገሙ — መደበኛ ሳሙናና ሻምፖ አይጠቀሙ:: **CHG ብቻ ይጠቀሙ::**

---

## የጸጉር ማስወገድ መመርያዎች

- ቀዶ ጥገናውን ካደረጉ በኃላ ባሉት 24 ሰዓታት ጸጉርዎን አይላጩ ወይም ጸጉር የማስወገጃ ዕቃዎች አይጠቀሙ—CHG አዲስ ለታለጨ ጸጉር ሊ.sያስከክ ይችላል::
- መላጨት ካለብዎት CHG ከመጠቀምዎ **በፊት** እና ከቀዶ **ጥገና ህክምናዎ 24 ሰዓታት በፊት** ያድርጉት::
- አስፈላጊ ከሆነ የቀዶ ጥገና ቡድንዎ በቀዶ ጥገና ክፍል ውስጥ ማንኛውንም የፀጉር ማስወገጃ ያካሂዳል::

# ሲደርስዎ ማድረግ ስላለብዎት ነገር ያቅዱ

## 1. ትራንስፖርቴሽን ያዘጋጁ

- **ወደ ቤትዎ የሚመልስዎት ትራንስፖርቴሽን ያቅዱ፡፡** ለደህንነትዎ ሲባል **ከማስታገሻ መድኃኒት ወይም ከማደንዘዣ በኋላ ብቻዎን መኪና መንዳት ወይም የሕዝብ መጓጓዣ መጠቀም የለብዎትም**፡፡ ኃላፊነት የሚሰማው አዋቂ ሰው ወደቤትዎ ሊመልስዎት ይገባል፡፡ ታክሲ ወይም የጋራራይድ የሚጠቀሙ ከሆኑ ሌላ አዋቂ ሰው ከእርስዎ ጋር መጓዝ ይኖርብዎታል፡፡ ከቀዶ ጥገና ህክምናዎ በኃላ ባሉት መጀመርያ 24 ሰዓታት አዋቂ ሰው ከእርስዎ ጋር እንዲቆይ በጥብቅ እንመክራለን፡፡

- **ታካሚው ከእንክብካቤ ጋር የተያያዘ ውሳኔ መወሰን የማይችሉ ከሆነ** አዋቂ ከጎናቸው ሊሆንና ያሉትን የፈቃድ ቅፆችን መሙላት ይኖርበታል፡፡

## 2. የህጻን እንክብካቤ ከማድረግዎ በፊት ያቅዱ

ህጻናት ራሳቸው ታካሚ ካልሆኑ በስተቀር የቀዶ ህክምና በሚደረግበት ቦታ ላይ መገኘት የለባቸውም፡፡ ሂደቱ በሚካሄድበት ስፍራ አንድ የቤተሰብ አባል ብቻ ከእርስዎ ጋር ይሆናል፡፡ የቀዶ ጥገና በሚያደርጉበት ቀን እባክዎ ጎብኝዎችን ይቀንሱ፡፡ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት inova.org/visitor ይጎብኙ፡፡

## ቀጠራዎን መቀየር ከፈለጉ ወይም ከታመሙ ምን ያደርጋሉ

- **ቀጠሮ ለመቀየር ወይም ሂደቱን ለመሰረዝ** በተቻለ መጠን በፍጥት ቀዶ ጥገና ሀኪሞን ያግኙ፡፡

- **ከቀዶ ህክምናው በፊት ባሉት 48 ሰዓታት ውስጥ የመተንፈሻ አካል ምልክቶች (እንደ ጉንፋን፣ ትኩሳት፣ የማይቆም ሳል ወይም ኢንፌክሽን) ከተከሰተብዎት** ለደህንነትዎ ሲባል የቀዶ ህክምናው ቀጠሮ እንቀይራለን፡፡ ከቀዶ ህክምናዎ በፊት ህመም ወይም ትኩሳትከተሰማዎት የቀዶ ህክምና ዶክተርዎ ጋር ይደውሉ፡፡ ቀዶ ጥገና እስሚደርጉበት ቀን አይጠብቁ፡፡

- **ምልክቶቹ በሳምንቱ መጨረሻ ቀናት ወይም ቢሮው ዝግ በሚሆንበት ቀን ከመጀመርዎ** ከስራ ሰዓት ውጭ በሚጠቀሙበትን የስልክ ቁጥር ይደውሉ ወይም በመመሪያዎ ውስጥ በተሰጠው ቁጥር የእንክብካቤ ቡድንዎን ያነጋግሩ፡፡

# በቀዶ ህክምናዎ ቀን ምን ያደርጋሉ

## 1. ምን ይዘው ይምጡ

- ሕጋዊ መታወቅያ፣ የመድህን ካርድ፣ ፋርማሲ ካርድ እና ክፍያ የሚከፍሉበት መንገድ (ቼክ፣ ጥሬ ገንዘብ ወይም ክሬዲት ካርድ)፡፡
- ካልዎት የቅድመ ህክምና ፍላጎት መግለጫዎን በ MyChart ወይም በኢሜይል (acpsubmission@inova.org) ይላኩ፡፡ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት inova.org/advancedirective ይጎብኙ፡፡
- የጀርባ ማዳመጫ መሳርያዎች ስምዎን እና የትውልድ ቀንዎ የያዘ መለያ ያለበት ማስቀመጫ ይዘው ይምጡ፡፡
- መነጸሮችን ለማዘዝ ጉዳዩን ያምጡ፡፡ እባክዎትን ኮንታክት ሌንስ እቤትዎ ያስቀምጡት፡፡
- CPAP ወይም BiPAP ማሽን የሚጠቀሙ ከሆነና ተከታትለው ሂደቱን ለማካሄድ ቀጠሮ ካሎት ይዘዋቸው ይምጡ፡፡ ወደ ሆስፒታሉ የሚገቡ ከሆነ Inova ጊዝያዊ ክፍል የምናዘጋጅሎት ይሆናል፡፡

## 2. ምን ይለብሳሉ

- ሰፋ ያሉና ምቹ ልብሶችን ይልበሱ፡፡
- ሁሉንም ጠቃሚ ነገሮችና ጌጣጌጦች በቤትዎ ውስጥ ያስቀምጡ፡፡ ከመጡ በፊት ሁሉንም ቀለበቶች እና ጌጣጌጦችን ያስወግዱ፡፡

## 3. መድሀኒት መመርያዎች

ለደህንነትዎ ሲባል ታካሚዎች በሆስፒታል የጤና እንክብካቤ ቡድናቸው ካልታዘዙ በስተቀር ከቤት ወይም በሌላ ሕክምና አቅራቢ የታዘዙ ማንኛውንም መድኃኒቶች ይዘው መምጣት ወይም መጠቀም የለባቸውም፡፡

ይህ የሚከተሉትን የሚያካትት ሲሆን በእነዚህ ግን የተወሰነ አይደለም

- የታዘዙ መድሃኒቶች
- ያለ ሀኪም ትእዛዝ የሚገዙ መድሃኒቶች (እንደ aspirin፣ ibuprofen፣ acetaminophen፣ Zyrtec፣ Claritin ወይም የአስም መድሃኒት)
- ሄርባል ወይም አማራጭ ቴራፒታት

በ ቆይታዎ ወቅት አስፈላጊ መድኃኒቶች ሁሉ የሆስፒታሉ ቡድን ያዝዛል፣ ይመረምራል እንዲሁም ትክክለኛነታቸውን ያረጋግጣል፡፡ ማንኛውንም ጥያቄ ካልዎት የህክምና ቡድንዎ ያናግሩ፡፡

# ከቀዶ ጥገናዎ በኃላ ምን ይጠብቃሉ

ከቀዶ ጥገናው በኃላ ወደ ማገገሚያ ክፍል ይወሰዳሉ፤ እዚያም ቡድናችን በሚነቁበት ወቅት ሁኔታዎን ይከታተላሉ፡፡ አብዛኛዎቹ ታካሚዎች በ2 እስከ 4 ሰዓታት ውስጥ ወደ ቤት ይሄዳሉ፤ ነገር ግን የማገገሚያ ጊዜዎ እንደ ተደረገልዎት ቀዶ ጥገና እና የሚኖርዎትን ስሜት በመመስረት ሊረዝም ይችላል፡፡

- ከመውጣትዎ በፊት የመውጫ መመሪያዎችዎን ከእርስዎ እና ወደ ቤት የሚወስድዎት አዋቂ ሰው ጋር እንመለከታቸዋለን፡፡ ስለ መድኃኒቶች፣ ቀጣይ እንክብካቤ እና በቤት ውስጥ ማገገምዎን እንዴት መቀጠል እንደሚችሉ መረጃ ይሰጥዎታል፡፡

- ቀዶ ጥገናውን የሚካሂዱበት ቦታ ፋርማሲ ካለው ወደ ቤት ከመሄድዎ በፊት የታዘዙልዎትን መድኃኒቶች እዚያው ማግኘት ይችላሉ፡፡

# ለቀዶ ጥገና መክፈል

ከቀዶ ጥገናዎ በፊት የ Inova ታካሚ የፋይናንስ አግልግሎት የሚያደርገው፡

- ያሉት ሽፋኖችና ጥቅሞች
- ከኢንሹራንስዎ አስፈላጊ ፈቃድ ማግኘት
- የሚኖርብዎት የፋይናንስ ወጪ እንዲገነዘቡ ማገዝ
- ማንኛውንም የፋይናንስ ማስተካካያዎች ማድረግ

እርስዎን ማግኘት ካልቻልን እባክዎ በቀዶ ጥገናዎ ቀን ማንኛውንም ተፈጻሚ የሚሆን የትብብር ክፍያ ወይም የጋራ ክፍያ ለመክፈል ይዘጋጁ፡፡

### ከቀዶ ህክምናዎ በኃላ ከአንድ በላይ የክፍያ ደረሰኝ እንደሚደርስዎት ይጠብቁ

በመጀመሪያ ከቀዶ ጥገናዎ ጋር ተያይዘው ለሚሰጡ አገልግሎቶች የኢንሹራንስ ክፍያ ጥያቄ እናቀርባለን፡፡ የኢንሹራንስ እቅድዎ ቀሪ ሂሳብ ካለው የተጋራ ክፍያ ወይም የኢንሹራንስ ድርሻ የክፍያ ደረሰኝ ይደርስዎታል፡፡

በተጨማሪም በእንክብካቤዎ ውስጥ ከተሳተፉ የተለያዩ አገልግሎት ሰጪዎች በርካታ የክፍያ ደረሰኞች ሊደርሱዎት ይችላሉ፤ እነዚህም ሆስፒታሉ ወይም የቀዶ ሕክምና ማዕከሉ፣ ቀዶ ሐኪምዎ እና ማደንዘዣ ባለሙያዎ ሊያካትቱ ይችላሉ፡፡

- **የሆስፒታል ወይ የቀዶ ጥገና ማዕከል የክፍያ ደረሰኝ፡** ይህ የተቋሙ የክፍያ ደረሰኝ ለሆስፒታሉ ወይም ለቀዶ ሕክምና ማዕከሉ የሚደረገውን ክፍያ ይሸፍናል፤ ይህም በእንክብካቤዎ ወቅት ጥቅም ላይ የዋሉ ሰራተኞችን፣ አቅርቦቶችን እና መሳሪያዎችን ያካትታል፡፡
- **የቀዶ ህክምና ዶክተር ደረሰኝ፡** ስለዚህ ሂሳብ ጥያቄ ካልዎት በሂሳብዎ ላይ ስሙን የተገለጸው የቀዶ ህክምና ሐኪም ያናግሩ፡፡
- **የማደንዘዣ ባለሙያ የክፍያ ደረሰኝ፡** ይህ ደረሰኝ bቀዶ ጥገናዎ ወቅት ለተሰጠዎት የማደንዘዣ አገልግሎት ይሸፍናል፡፡ ስለዚህ የክፍያ ደረሰኝ ጥያቄ ካለዎት በደረሰኝዎ ላይ የተጠቀሰውን የማደንዘዣ ቡድን ያነጋግሩ፡፡
- **የውበት ቀዶ ህክምናዎች፡** የኮስሞቲክስ ቀፎ ጥገናዎች ቀደም ብለው መከፈል ይኖርባቸዋለ፡፡

### የክፍያ ደረሰኝ እና የዋጋ ተመን የሚመለከቱ ጥያቄዎች?

- ለሚኖርብዎት ጥያቄ ወይም ክፍያዎች ወደ Inova **ታካሚ ፋይናንሻል አገልግሎቶች** በ571-472-5750 ይደውሉ፡፡
- ተመን የሚመለከቱ ጥያቄዎች Inova **ዋጋ ተመን ድጋፍ ቡድን ፋይናንሻል አገልግሎት** በ571-472-3300 ይደውሉ፡፡

በ MyChart የራስዎን ግምት ማዘጋጀት ይችላሉ፡፡ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት inova.org/hospitalcharges ይጎብኙ፡፡

## የፋይናንስ ድጋፍ ይፈልጋሉ?

Inova የሕክምና ክፍያቸውን ለመክፈል እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ታካሚዎች በ MyChart፣ በፖስታ ወይም በአካል በመገኘት የፋይናንስ ድጋፍ ይሰጣል፡፡ ለበለጠ መረጃ የ Inova የፋይናንስ እርዳታ ቡድንን በ571-472-5880 ይደውሉ ወይም www.inova.org/patient-and-visitor-information/financial-assistance ይጎብኙ፡፡

# ቦታዎች

## Alexandria አካባቢ

**[Inova Alexandria Hospital Surgery Center]**
4320 Seminary Road
Alexandria, VA 22304
703-504-3000
ተጨማሪ መረጃ፡ www.inova.org/locations/inova-alexandria-hospital-surgery-center

**Inova Mount Vernon Hospital Surgery Center**
2501 Parkers Lane
Alexandria, VA 22306
703-664-7000
ተጨማሪ መረጃ፡ www.inova.org/locations/inova-mount-vernon-hospital-surgery-center

---

## Annandale/Falls Church/Fairfax (Inova Fairfax Medical Campus)

**Inova Woodburn Surgery Center**
3289 Woodburn Rd, #130
Annandale, VA 22003
571-472-7030
ተጨማሪ መረጃ፡ www.inova.org/locations/inova-woodburn-surgery-center

**Inova Fairfax Hospital Surgery Center**
Inova Fairfax Medical Campus
3300 Gallows Road
Falls Church, VA 22042
703-776-5900
ተጨማሪ መረጃ፡ www.inova.org/locations/inova-fairfax-hospital-outpatient-surgery-center

**Inova Professional Services Building – Surgery Center**
Inova Fairfax Medical Campus
3300 Gallows Road
Falls Church, VA 22042
703-776-6630
ተጨማሪ መረጃ፡ www.inova.org/ifmc/psb-sugery

**Inova Saville Cancer Screening and Prevention Center**
8081 Innovation Park Dr, Pavilion - Level P1
Fairfax, VA 22031
571-472-3500
ተጨማሪ መረጃ፡ www.inova.org/locations/inova-saville-cancer-screening-and-prevention-center

## Fair Oaks አካባቢ

**Inova Fair Oaks Hospital Surgery Center**
3600 Joseph Siewick Drive
Fairfax, VA 22033
703-391-3600
ተጨማሪ መረጃ፡ www.inova.org/locations/inova-fair-oaks-hospital-surgery-center

## Leesburg/Loudoun አካባቢ

**Inova Loudoun Hospital Surgery Center**
44045 Riverside Pkwy
Leesburg, VA 20176
703-858-6490
ተጨማሪ መረጃ፡ www.inova.org/locations/inova-loudoun-hospital-surgery-centers